# የኢንዱስትሪ ልማት ሥትራቴጂያችንን ትክክለኛነት ያረጋገጠው የስትራትፎር ጥናት

**ዮናስ 08/13/13**

ስትራትፎር የተሠኘውና ቀዳሚ የመልካዓምድራዊ ፖለቲካ የስለላ ተቋም ከሰሞኑ "sixteen countries tipped to succeed china" የቻይና ኢኮኖሚ ማሽቆልቆልና በእግሯ የሚተኩ 16 ሃገራት የሚል ጥናት የተቋሙ መስራች በሆነው ጆርጅ ፎርድ ማን በኩል በጡመራ(blog) ገጽ አስነቡቧል፡፡

ጥናቱ በመግቢያው ላይ እንዳስነበበው ከሆነ the group named the "pc16" or the post china 16" by geopolitical intelligence firm and report authors, stratfor, includes countries as disparate as Ethiopia, Cambodia and Mexico. የቻይና ኢኮኖሚ ችግሮች pc16 ወይም ድህረ ቻይና 16 ለሆኑ ባተሌ ሃገሮች ማለትም ከኢትዮጵያ እስከ ካምቦዲያና ሜክሲኮ ያሉ በዓለም ግንባር ቀደም የፋብሪካ አምራቶች እንዲሆኑ ዕድል ይከፈትላቸዋል፡፡

Between April and June the world's second biggest economy grew by 7.5% compared to the previous year, down. from 7.7% in January to march period. ….. the era of Chinese development predicated on low wages to coquer global markets is ending because these are new other nation with even lower wages and other advantages such as political stability and demographics.

ከጥር እስከ ሠኔ የአለምን ኢኮኖሚ በብቸኝነት በ7.5 ስትመራ የቆየችው ቻይና ከቀደሙት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ኢኮኖሚያዊ በ7.7 በመቶ እየወረደ ነው፡፡እንደ ስትራትፎር ጥናት ቻይና በአሁኑ ሰዓት በዝቅተኛ ደመወዝ ክፍያ እርከንና ከፍተኛ ዕድገት ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ባላቸው ርካሽ የሠው ጉልበትና በርካታ አምራች ወጣት ሃይል እንዲሁም በሃገራቸው በሚታይ ፖለቲካዊ መረጋጋት በሚቀጥሉት ጊዜያት ኢትዮጵያን ጨምሮ በተቋሙ ስያሜ pc16 የተባሉት የአለም ሃገራት በቻይና የበላይነት ተይዞ የነበረውን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የበላይነት ይቆጣጠሩታል ይላል ጥናቱ፡፡ ጥናቱ ጨምሮም እነዚህ ሃገራት ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡባቸው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በተለይም የጫማ ምርት፣ የሞባይልና የጨርቃጨርቅ እንደሆኑም አመልክቷል፡፡

ከቻይና ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ጋር በተያያዘም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች  ሃገራችን ስትራትፎር በጠቆማቸው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በአለም ግንባር ቀደም ሚና የምትጫወትበት ጊዜ ላይ መድረሷ አስቀድሞ ሳይታለም የተፈታ እንደሆነ ደግሞ ከቻይና ኢኮኖሚና ከላይ ከተመለከተው የስትራትፎር የጥናት መረጃ አኳያ የኢንድስትሪ ልማት ሥትራቴጂያችንን መፈተሹ ተገቢ ይሆናል፡፡

እንደ እስትራትፎር ጥናት ከሆነ ኢትዮጵያን ጨምሮ በጥናቱ የቻይናን ኢኮኖሚ በትብብር ይተካሉ ተብለው ይፋ የሆኑት ሃገራት ያላቸው ርካሽ የሠው ጉልበትና በርካታ አምራች ወጣት ሃይል እንዲሁም ፖለቲካዊ መረጋጋት በምክንያትነት ቀርቧል፡፡ ስለሆነም በጨርቃጨርቅ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች እንዲሁም በሞባይል አምራችነት የአለምን ኢኮኖሚ ይቆጣጠራሉ፡፡

የአገራችን የልማት እንቅስቃሴና ልምድ የኢኮኖሚ ሳይንስ የሚያስቀምጣቸው መሰረታዊ ድምዳሜዎች መሰረት በማድረግ ፈጣን ልማትንና ቀልጣፋ የሃብት ድልድልን ለማረጋገጥ እንዲቻል ካፒታልን የሚቆጥብና የሠራተኞች ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የልማት አቅጣጫ እንዲሆን የተደረገው በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ስርዓት መመራት ስንጀምር ነው፡፡

ከዚህም በመነሳትም ካፒታልን በላቀ  ደረጃ ለመቆጠብና የሠራተኛ ጉልበትን በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችለው ዋነኛ አማራጭ ግብርና በመሆኑ ግብርናን ማዕከል ያደረገ የኢንዱስትሪ ልማት ሃገሪቱ የምትከተል መሆኑም አስቀድሞ የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታወስ የሚገባው አንድ ጉዳይ አለ፡፡ይኸውም ኢንዱስትሪ በአጠቃላይ ከግብርና ጋር ሲነፃፀር ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀምና በተነፃፃሪ ደግሞ የሰራተኛ ጉልበትንበሰፊው የማይጠቀም የመሆኑ ጉዳይ ነው። አንዳንዶች ፖሊሲውን የሚያብጠለጥሉትም  ይህንኑ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ አንዳንድ በኢንዱስትሪ ዘርፍም ካፒታልን ቆጥቦ ጉልበትን በሰፊው በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው ዘርፎች መኖራቸውንም  እዚህ ጋር መዘንጋት አይገባም፡፡

ለምሳሌ የልብስስፌትና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ካፒታልን በላቀ ደረጃ ቆጥቦ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም ሲሆን የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ ደግሞ የዚህ ግልባጭ ነው። ስለሆነም በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሃብት ድልድልን ቀልጣፋነት መሰረት ያደረገ የዘርፍ ምርጫ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት መንግስት የኢንዱስትሪ ልማታችን ግብርና መር መሆን እንዳለበት ብቻ አስቀምጦ ሳያበቃ ለግብርና የሚሆን ግብአትና እቃዎች በማቅረብና የግብርና ምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ ለገበያ በማቅረብ (አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ) ላይ ማተኮር እንዳለበት አስቀምጧል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ትኩረት የሚሻና የግድ የሆነ ተጨማሪም ጉዳይ አለ፡፡ይኸውም ይህንኑ ልማት ፈጣንና አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስችል በአለም ገበያ የመወዳደር ብቃትን የሚያረጋግጥ ጉዳይ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአገራችን ኩባንያዎች አሁን ባላቸው የካፒታል መጠንና የቴክኖሎጂ አቅም በአለም ደረጃ በፍጹም መወዳደር አይችሉም፡፡ የአገራችን ኩባንያዎች ሊኖራቸው የሚችለው ብልጫና የመወዳደር አቅም በርካሽና በታታሪ የሰራተኞች ጉልበት ነው፡፡

ኤክስፖርት መሪ የሆነ የኢንዱስትሪ ልማት እንከተል፤ በአለም ገበያ የመወዳደር ብቃት ያለው ኢንዱስትሪ የመገንባት አላማችን ሊሳካ የሚችለው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቅም ኢንዱስትሪ ላይ በማተኮር ነው የሚባለውም ለዚህና በካፒታልና በቴክኖሎጂ ያለብንን ብልጫ ለማካካሥ ነው፡፡

አሁንም እንደገና ከላይ የተጠቀሱትን ብቻ በማሟላት ብቁ ተወዳዳሪ መሆን የማያስችለንና ትኩረት የሚሰጠው አንድ ጉዳይ አለ፡፡

ይኸውም የሚኖረው ችሎታና ምርታማነት ነው፡፡ የእያንዳንዱ ሠራተኛ የማምረት ችሎታና ታታሪነት የላቀ መረጃ ላይ ካልደረሰ በስተቀር በርካሽ ጉልበት ብቻ መወዳደር እንችላለን ማለት አይደለም፡፡ርካሽ ጉልበት ያለን እኛ ብቻ አይደለንም፤ በተነፃፃሪ ከኛ የተሻለ ርካሽ ጉልበት ያላቸው ብዙ ሃገሮች እንዳለ ሊሠመርበት ይገባል፡፡

በስትራትፎር ጥናት እንደተመለከተውም የአለምን ¼ ህዝብ የያዙት ህንድና ቻይናም ርካሽ ጉልበት በገፍ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ቻይናን የገጠማት ጉዳይ የርካሽ ጉልበት ሳይሆን የምርታማነትና በዚያ ልክ የሚከፈል ዋጋ አለመመጣጠን ነው፡፡ በሌላ መልኩ በአለም ላይ ርካሽ ጉልበት ካላቸው በርካታ ሃገሮች በስትራትፎር ጥናት መሰረት ቻይናን ይተኳታል የተባሉት ሃገራትም ርካሽ ጉልበት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቻይና ያጎደለችውን ምርታማነትና ተመጣጣኝ የጉልበት ዋጋ መሙላት በመቻላቸው እና ቻይና ያጎደለችውን የፖለቲካ ጉዳይ ጎን ለጎን መሙላት በመቻላቸው ነው፡፡

ባይሆንማ ኖሮ ከኛም ሆነ በስትራትፎር ጥናት ቻይናን ይተካሉ ከተባሉት 16 ሃገራት በላይ የሰው ጉልበትና ሌሎችም ግብአቶች ያሏቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ጉዳዩ ግን የምርታማነት እና ተገቢ የጉልበት ዋጋ እንዲሁም የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት በመሆኑ ይህንን ጥያቄ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲያችን አስቀድሞ የመለሰ መሆኑና በተግባርም የተረጋገጠ በመሆኑ ጥናቱ ትክክለኛና የፖሊሲያችንን ውጤታማነትም ያስመሰከረ ነው ለማለት ያስችላል፡፡

ጉዳዩን መጠነ ሰፊ የሰው ሃይል ካላት ቻይና፣ ይህንኑ ተጠቅማ ላለፉት አመታት የአለምን ኢኮኖሚ በሁለተኝነት ደረጃ ስትመራ ከመቆየቷና አሁን ከመንሸራተቷ አንፃር አፍታተን እንየው፡-

ቻይና ባለፉ 30 ዓመታት አስደናቂ የኢኮኖሚ እድገት ማሣየቷ በርግጥም ሃቅ ነው፡፡ አሁን ግን ይህን እድገት ማስቀጠል እየተሣናት እንደሆነ የስትራትፎር ጥናት ያረጋግጣል፡፡ ያለፉት 30 ዓመታት የቻይና ኢኮኖሚ ምጥቀት በአስተዛዛቢ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ የሚያወሣው ጥናት እንደሚለው ከሆነ ቻይና በገነባቻቸው ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞቿ የምትከፍለው ደመወዝ እንደምዕራባውያን ሃገሮች አይደለም፡፡ በዚህም የተነሣ ምርቷም ርካሽ ነው፡፡

ይህን ምቹ አጋጣሚ ያጤኑቱ ምዕራባውያን ኢንቨስተሮች ደግሞ ወደቻይና ዘምተዋል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በቻይና የሚመረቱትን ምርቶች የቻይና ዜጎች አብዛኛውን ስለማይሸምቱ ምርቶቹ ወደውጭ ይላካሉ፡፡ ስለሆነም የቻይና ኢኮኖሚ የተገነባው የሃብት ድልድልን ውጤታማነት መሠረት ባደረገና ምርትና ምርታማነትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሣይሆን ርካሽ ዋጋ ባላቸው የኤክስፖርት ንግዱ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምርቷን የሚጠቀሙ ደሃ ሃገራት ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ ላለፉት 30 ዓመታት አዝልቋታል፡፡

አሁን ግን ርካሽ የሠው ጉልበት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቻይና የተሻለ ፖለቲካዊ መረጋጋት ያላቸው ሃገራት ቀስ በቀስ ወደ አለም አቀፍ መድረክ እየመጡ መሆናቸው ቻይና በሄደችበት መንገድ መጓዝ እንደማያዋጣትና ፖሊሲዋን ልትፈትሽ የሚያስገድዳት ደረጃ ላይ እንድትገኝ ከማድረጉም በላይ ሃገራችንን ጨምሮ እነዚህ በቻይና እግር ይተካሉ የተባሉት ሃገራት ባላቸው ርካሽ ጉልበት ላይ የሃብት ድልድልን ውጤታማነት እና ለምርትና ምርታማነት ቅድሚያ ሠጥተው ወይም ታሣቢ አድርገው መንቀሣቀሣቸው በቻይና ኢኮኖሚ ከመተካታቸውም በላይ ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ዕድላቸው የሠፋ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ቻይና እየተከሠተባት ያለው የሥራ አጥነት ሥፋትና ከሠራተኛ ደመወዝ ጋር የተያያዘው ውስብስብ የሰብአዊ ችግር መነሻ እነዚሁኑ ነጥቦች ታሣቢ ያላደረገ የውጭ ኢንቨስትመንት አለመከተሏ ነው፡፡ በእኛ ሃገር ተጨባጭ ሁኔታ ይህንንና የቻይናን ዓይን ላለፉት 30 ዓመታት ጋርዶ አሁን ላይ የመጣውን ዕዳ ለማወራረድ ያስቸገራትን ጉዳይ ላለማስተናገድ ሲባል የምንከተለው አቅጣጫ የሃገር ውስጡንና የውጭውን ባለሃብት አቀናጅቶ የመጠቀም አቅጣጫ ነው፡፡

የሃገሩ ውስጥ ባለሃብት ኢንቨስትመንት ያለው ዘላቂ የሆነ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ የካፒል እጥረት ባለባት ሃገራችን የውጭ ባለሃብቱ የተትረፈረፈ የካፒታል ክምችት የካፒታል

እጥረትን በመቅረፍ የኢንዱስትሪ ልማታችንን ማፋጠን የመቻሉ እውነት ለውጪው ኢንቨስተር በራችንን የመክፈታችን የመጀመሪ ምክንያት ነው፡፡ የዓለም ገበያን ሰብሮ የመግባት ልምድና ችሎታው በሌላት አገራችን የውጭው ባለሃብት ጠንካራ ዓለማዊ የገበያ መረብ የውጭ ገበያውን ሠብረን ለመግባት የቀለለ መረማመጃ ሆኖ ሊያገለግለን የመቻሉም ጉዳይ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የአመራር ብቃት ጉድለት በማይታይባት ሃገራችን የውጭው ባለሃብት የዘመናዊ አመራርና አጠቃቀም ችሎታውን ሊያስተላልፍልን መቻሉም ተያያዥ የሆነ አብይ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም ነው የውጭው ባለሃብት ሊያስገኝልን የሚችለውን ከላይ የተመለከቱ ጥቅሞች አሟጦ ከመጠቀም ውጭ እንደቻይና ወደኋላ የማይመለስና ባለበት የማይቆም ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት ማረጋገጥ አይቻልም የሚባለው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭው ባለሃብት በአገራችን ኢንቨስት ሲያደርግ  በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን አማራጮች ፈትሾና በይበልጥ የሚጠቅመው መሆኑን አረጋግጦ ስለመሆኑ በመገንዘብና ከሌሎች የመወዳደሪያ አቅሞቻችን  ጨምሮ ዋነኛ መወዳደሪያ አቅማችን የሆነውን የሰለጠነ ታታሪና ርካሽ የሠራተኛ ጉልበት በተመለከተ የሠራተኛ ደመወዝ እድገቱ ጎን ለጎን መጨመሩ የማይቀርና ተገቢ መሆኑንም የሚገነዘበው  የውጭ ባለሃብት አንድ ወቅት የተሻለ ወደሚለው ሃገር መሄዱ የተለመደ በመሆኑ በተለይም የውጭው ባለሃብት የተሠማራበት መስክ ለሃገራችን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት ወሳኝ የሆነ ዘርፍ ከሆነ የልማታችን ፍጥነትና ቀጣይነት ልክ እንደ ቻይና ለከፍተኛ አደጋ ሊጋለጥ የሚችል መሆኑን በማስመር ከላይ የተጠቀሱትን የውጭ ኢንቨስትመንት ጠቀሜታዎችን ታሣቢ በማድረግ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን ከረጅም ጊዜ አኳያ እነኚህን ደካማ ጎኖች ለመቅረፍ በሚያሥችል፣ ከዓጭር ጊዜ አኳያ ደግሞ እነዚህን እጥረቶች በተለያዩ መንገዶች፣ የውጭውን ባለሃብት በመጠቀም ጭምር ለማካካስ የሚያስችል ሆኖ የተሠራ መሆኑና ይህም በተግባር እየተተረጎመ መሆኑ ነው በዘርፉ የምንገኝ በተደራጀና ወደዓለም አቀፍ  መድረክ ብቅ የማለታችንን ቀጣይነትና ዘላቂነት ስትራትፎር እንዲያረጋግጥ ያደረገው፡፡

ብዙዎቹ የምጣኔ ሃብታዊ ሳይንስ ጠበብቶች እንደሚገልጹት የጨርቃጨርቅና የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪን በመነሻነት ሳይጠቀም በኢንዱስትሪ የበለፀገ አገር የለም፡፡ ኢንዱስትሪው በመሠረቱ ጉልበትን በሠፊው የሚጠቀም መሆኑና ልብስ ከምግብ ቀጥሎ እጅግ ተፈላጊ የሆነ ሸቀጥ በመሆኑ ምንጊዜም ሠፊ የገበያ እድል ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ሃገራችን በኢንዱስትሪ መበልፀግ የጀመረችና ግን ደግሞ የካፒል እጥረት ያለባት መሆኑን ከግምት በመክተት  ይህንን ካፒታል በመቆጠብ ጉልበትን በሠፊው የመጠቀም ኢንዱስትሪን፣ በተጨማሪም ሠፊ ገበያ ያለውን ኢንዱስትሪ መሠረት ማድረጓ ትክክልና ተገቢነት ያለው ነው፡፡

በመግቢያዬ አካባቢ እንዳመላከትኩት የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን የኢንዱስትሪ ልማታችን ከግብርና ልማት ጋር መያያዝ እንደሚኖርበት አፅንኦት ይሠጣል፡፡ የጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ኢንዱስትሪ አንዱና መሠረታዊ ግብአት የሆነው ጥጥ በአገራችን የሚመረትና እጅግ በተሻለ ጥራትና መጠንም ሊመረት የሚችል መሆኑ ግብርናና ኢንዱስትሪ ተመጋግበው እንዲያድጉ ሠፊ ዕድል የሚሠጥ ነው፡፡

ከዚህ በመነሣት ማረጋገጥ የሚቻለውየጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ኢንዱስትሪ በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን ላይ የተቀመጡትን መሠረታዊ መርሆዎች የሚያሟላ መሆኑን ነው፡፡ ካፒታልን ቆጥቦ፣ ጉልበትን በሰፊው ይጠቀማል፡፡ የሥትራፎር ጥናት እንዳመለከተውም በግብርና ምርቶች ለይ እሴት የመጨመር ሥራን ይሠራል፡፡

በኤክስፖርት ገበያ ለመወዳደርና በቻይና እግር ለመተካትም እድል ይሠጣል፡፡ ይህ ደግሞ ከወረቀት አልፎ መሬት ላይ ያረፈ መሆኑና በተጨባጭ የኢንቨስተሮችን ቀልብ መሣብ መቻሉ የስትራትፎር ጥናት የፖሊሲያችንን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሌላውና በስትራትፎር ጥናት መሠረት በቻይና እግር የሚተኩት 16 ሃገራት የሚሳተፉበት የኢኮኖሚ መስክ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ነው፡፡ ልክ እንደጨርቃጨርቁ ሁሉ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ካፒታልን የሚቆጥብና ጉልበትን በሠፊው የሚጠቀም ኢንዱስትሪ በመሆኑ ሃገራችንም ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሠጥታ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ መሠረት በጫማ ሥራ (የቆዳም ሆነ የሸራ) ሠፊ ገበያ ያለውና በሠፊው ገብተን ለመወዳደር በሚያስችለን ደረጃ ላይ መድረሣችንና ይልቁንም በመጨረሻ ደረጃ የተዘጋጀ ቆዳን ከውጭ እያስገባንና በጫማና በሌሎች የስፌት ስራዎች እሴት ጨምረን ኤክስፖርት ማድረግ መጀመራችን የውጭ ባለሃብቱን ትኩረት የመሣባችን እውነትነት ነው ስትራትፎር ሃገራችንን በቻይና እግር ከሚተኩ ሃገራት መካከል ለመምረጥ ያስቻለው።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው ባለንበት ዓለም ጥብቅ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲፈጠር ካደረጉት ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ አማካኝነት በዓለም የተለያዩ ጫፎች ያሉ ፋብሪካዎች በአንድ ቦታ የተሠባሠቡ ይመስል በጥብቅ ተቀናጅተው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ልማታዊ የሆነው መንግስታችን ለልማት ቆርጠው የተነሡ አገራት እንደሚያደርጉት ሁሉ በአፋጣኝ መላው ዜጋ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ በተያያዝነው ልማትና ባለንበት ዓለም ውስጥ ተዋናይ መሆን ወይም አለመሆንን ከሚወስኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ የቴሌ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መሆኑንም በመገንዘብ መንግስት ዘርፉን በኔትወርክ ግንባታና በአፓራተስ ምርት ትኩረት ሠጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የቴሌ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሃገራችን በመላ እንዲዳረስ ማድረግ በአገራችን ውስጥና በአገራችን እና በአለም ገበያ መካከል ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ ለኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ኢንዱስትሪ ማበብ የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር፤ በዚሁ በመጠቀም በመላ አገሪቱ የሚካሄደውን የማህበራዊ አገልግሎትና የመንግስት ሥራ ጥራትና ቅልጥፍና የስርጭት አድማሡን ወዘተ በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል፣ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማታችንን በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብና በዚሁ ዘርፍ መንግስት ልዩ ትኩረት ሠጥቶ እየሠራ መሆኑ በተጨባጭ የሚታይ መሆኑ ሃገራችንም በሞባይል ምርቶች በቻይና እግር ልትተካ የምትችል እንደሆነ በስትራትፎር ጥናት ተመልክቷል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ሃገራችን የምትከተለው የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለግጭት መንስዔ የሆኑ አካባቢያዊና ሃገራዊ የስልጣን ሽሚያ መንጠራወዞችን ያስቀረና የጠረጋጋ የፖለቲካ አየር እንዲነፍስ ማስቻሉ፤ ህዝቡ በቀጥታ የሚወከልበት ምክር ቤት ፌደራላዊ ስርአቱን የሚያፀናው እያንዳንዱ ብሔረሰብ የሚወከልበት የፌደሬሽን ምክር ቤት መኖሩ ባልተማከለ አስተዳደራችን ህዝብ የስልጣን ባለቤት መሆኑ የፈጠረው መረጋጋት ኢትዮጲያን ተመራጭ ማድረጉ ሊሰመርበት ይገባል።